AMHARIC

የሲያትል ፖሊስ መምሪያ

# የ 9-1-1 የአስተርጓሚ
## አገልግሎትን ስለመጠቀም

የሚከተሉትን ሁኔታዎች ሲገጥሙ 9-1-1 ይደውሉ፦

- ■ አስቸኳይ የፖሊስ፣ የእሳት አደጋ ወይም የሕክምና ፍላጎት ሲኖር።
- ■ አሁን የተፈጸመውን ወይም እየተፈጸመ ያለውን ወንጀል ለማሳወቅ።
- ■ በሕይወት፣ በንብረት ወይም በሁሉቱም ላይ ጉዳት የሚያደርስ፣ ወይም ማድረስ የሚችል ሁኔታ ሲያጋጥም።
- ■ ወንጀል ነክ ለመሆኑ አጣራጣሪ የሆነ የሰው(ዎች) ወይም የመኪና ድርጊት።

**የ 9-1-1** አሠራር ትንሽ እንግሊዘኛ ቢችሉም ወይም በጭራሽ ባይችሉትም አስተርጓሚ አለው።

1. በመጀመሪያ እንደደውሉ፣ ምን ዓይነት አገልግሎት እንደሚፈልጉና በምን ቋንቋ እንደምናገሩ ይግለፁ።

"I need POLICE. I speak AMHARIC."
"ፖሊስ እፈልጋለሁ። አማርኛ እናገራለሁ።"

"I need the FIRE DEPARTMENT. I speak AMHARIC."
"የእሳት አደጋ መከላከያ እፈልጋለሁ። አማርኛ እናገራለሁ።"

"I need MEDICAL help. I speak AMHARIC."
"የሕክምና እርዳታ እፈልጋልሁ። አማርኛ እናገራለሁ።"

2. **የ 9-1-1** ሠራተኛ ከአስተርጓሚ ጋር ያገናኙዎታል፤ በማስተላለፊያው ሰዓት ብዙ ሴኮንዶች ሊዘገዩ ይችላሉ። በዚያን ጊዜ በስልኩ መስመር ላይ ይቆዩ።

3. አስተርጓሚው ብቅ ሲል፣ የሚጠየቁትን ጥያቄ ይመልሱ። በተቻለ መጠን በአጭሩ በቀጥታ ስለተከሰተው ነገር ይናገሩ።

AMHARIC

# የሲያትል ፖሊስ መምሪያ

## የ 9-1-1 የአስተርጓሚ አገልግሎትን ስለመጠቀም

4. የ 911 ሠራተኛ በሚሰጡት መረጃ በመመርኮዝ ውሳኔ ይሰጣሉ።ለሠራተኛው ለመናገር ዝግጁ ይሁኑ።

- ድንገተኛው አደጋ እየተከሰተ ያለበትን ቦታ፣ የሕንፃውን ቁጥር፣ የአፓርታማውን ቁጥር፣ የመንገዱን ስምና አቅጣጫውን (ይህም ማለት፣ ሰሜን ምዕራብ፣ ደቡብ ወዘተርፈ) ይጨምሩ።

- ስምዎን፣ አድራሻዎንና እየደወሉ ያሉበትን ስልክ ቁጥር ይናገሩ።

5. እስኪነገርዎት ድረስ ስልኩን አይዝጉ። መዘጋት እንደሚችሉ የስልክ ሠራተኛው እስኪነግርዎት ድረስ ስልኩን አይዝጉ።

ፖሊሶቹ በሚደርሱበት ጊዜ ለመግባባት አስተርጓሚ ከፈለጉ፣ ማቅረብ ይቻላል።

ልብ ይበሉ፦

- እራሴ ስልክ በምደውልበት ጊዜ 9-1-1 ነጻ ነው።

- ማንነትዎ እንዳይታወቅና መረጃው በሚስጥር እንዲሆን ከፈለጉ፣ ለሠራተኛው ይናገሩ።

- 9-1-1ን በድንገት ቢደውሉ፣ ስልኩን አይዝጉ! በስልኩ መስመር ላይ ቆይተው የደወሉት ሆን ብለው እንዳይደለ ይንገሩአቸው።

እ ኤ አ በ 2005 የሲያትል ፖሊስ መምሪያ ከሲያትል ነይበርሁድ ቡድን ጋር በመተባበር ያዘጋጀው ጽሑፍ።

www.seattle.gov/police

610 Fifth Avenue
P.O. Box 34986
Seattle, WA 98123-4986

Seattle Neighborhood Group
www.sngi.org

1806 East Yesler Way
Seattle, WA 98122-5748